# 2ኛ ትምህርት

*ከሰኔ 25 - ሐምሌ 1* *Jul 2 - 8*

## የተነጠቅነውን ግዛት ማስመለስ

### ሰንበት ከሰዓት

ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ዘፍ. 1:26— 28፣ መዝ. 8:3—8፣ ዘፍ. 2:15፣ ሮሜ 8:20—22፣ ዘፀ. 20:1—17፣ ሮሜ 1:25፣

2ተሰ. 3:10.

> **የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡-** "እግዚአብሔር 'ሰውን በመልካችን በአምሳላችን እንሥራ፤ በባሕር ዓሦች፣ በሰማይ ወፎች፣ በከብቶች፣ በምድር ሁሉ ላይ፣ እንዲሁም በምድር በሚሳቡ ፍጡራን ሁሉ ላይ ሥልጣን ይኑራቸው አለ' " (ዘፍ. 1:26)።

በመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን ላይ ውድቀት እንደ ተከሰተ ቀድሞ ተጎናጽፈውት ከነበረው አምላካዊ መልክ የላቀውን አጡ። "ሰው ብቻ ሳይሆን ምድርም በክፉው ቁጥጥር ሥርበመዋሏ በደኅንነት እቅድ መዋጀት ነበረባት። አዳም እንደ ተፈጠረ ምድርንና ሙላቷን የመግዛት ሥልጣን ተሰጥቶት ነበር። ሆኖም የቀረበለትን ፈተና በጽናት ማለፍ ባለመቻሉ በሰይጣን ኃይል ስር ወደቀና በሥልጣኑ ስር የነበረው ግዛት እርሱን ወደ ተቆጣጠረው አካል ተሸጋገረ። ይህን ተከትሎ ሰይጣን 'የዚህ ዓለም ገዢ' በመሆን፤ በመጀመሪያ ለአዳም ተሰጥቶ የነበረውን ምድራዊ ግዛት ያለ አግባብ ነጠቀ። ነገር ግን ክርስቶስ መሥዋዕት ሆኖ የኃጢአትን ቅጣት በመክፈል ሰብዓዊውን ፍጡር ብቻ ሳይሆን ሰብዓዊው ዘር አጥቶት የነበረውንም ግዛት አስመለሰ። በመጀመሪያው አዳም የታጣው ሁሉ እነሆ በሁለተኛው ሙሉ ለሙሉ ይመለሳል።"–Ellen G. White, in Signs of the Times, November 4, 1908.

ከውድቀት በኋላ ለእኛ ሰብዓዊ ፍጡራን በመጀመሪያ የተሰጠንን "ግዛት" ጨምሮ ስፍር ቁጥር የሌላቸውን አያሌ ነገሮች ማጣታችን እምብዛም አጠያያቂ አይደለም።

ለመሆኑ ይህ ያጣነው ግዛት ምን ነበር? ዛሬ፣ ዛሬ "ግዛት" የተሰኘው ጽንሰ ሃሳብ አረዳድ አሉታዊ አንደምታ ከማመዘኑ አኳያ በኤደን ገነት የነበረውን ሁናቴ

በትክክል ሲወክል አይስተዋልም፡፡ ሰብዓዊ ፍጡራን ያኔ በመጀመሪያ ምድርን እንዲገዙ ሥልጣን ተሰጣቸው የተሰኘው አባባል ፍቺ ምንድን ነው? በኤደን የነበሩት ወላጆቻችን ላይ የደረሰውን አሳዛኝ ክስተት ተከትሎ ካጣናቸው አንዳንዶቹን መልሰን የራሳችን ማድረግ እንድንችል ቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት እገዛ ማድረግ ትችላለች?

*እሁድ ሰኔ 26* *Jul 3*

## በምድር ላይ ሥልጣን እንዲኖራቸውና ምድርን እንዲገዙ ተፈጠሩ

በቅርቡ አንድ ሰው ስለ አንዲት ኢአማኒ ወዳጁ ሲጽፍ እንዲህ ብሎ ነበር "ሌሊት በድቅድቅ ጨለማ ብንን ስትል አንዳንድ ጥልቀት ያላቸው የህይወት ጥያቄዎች አእምሮዋን ያጨናንቁታል፡ 'በእርግጥ ይህ ምድር በግዙፉ ሕዋ በአጋጣሚ የተከሰተ የአንድ ትልቅ ፍንዳታ ውጤት ነው? ለሰብዓዊው ፍጡር በሕይወት መመላለስም ሆነ በአጠቃላይ ለግዙፉ ዩኒቨርስ እንዴት ራሱን የቻለ ንድፍም ሆነ እቅድ ሳይኖር ቀረ? የራሴን ጨምሮ የባለቤቴ፣ የሁለቱ ልጆቼም ሆነ የማንኛውም ሰው ሕይወት ሙሉ ለሙሉ እርባና ቢስና ትርጉም የለሽ ነው? ሕይወቴ ትርጉምም ሆነ ዓላማ ቢስ ነውን?' ከውድቀት በኋላ ሰብዓዊው ፍጡር ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ነገሮች አጥቶአል፡፡ የውድቀት ታሪክ እንደሚያሳየን ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ሳይሆን እርስ በርሳችንም ተለያይተናል--አንዱ ለሌላው ባይተዋር ሆኗል፡፡ ከምድር ጋር የነበረንም ግንኙነት ተለውጦአል፡፡ ከላይ በተጠቀሰችው ሴት በቀረበው ጥያቄ እንደተመለከተው ማንነታችንን ለማወቅም ሆነ በህይወት የመመላለሳችንን ዓላማ ለመረዳት ፍልሚያ እናደርጋለን፡፡ በፈጠረን አምላክ መታነጻችንንና በዓላማ ወደዚህ ምድር መምጣታችንን አርቆ መመልከት አለመቻል የሚፈጥረውን ብዥታ ተከትሎ--የህልውናችን መንስዔ አጋጣሚ ነው፤ የሚለው በስፋት እየናኘ ያለው አመለካከት ለብዙዎች ብርቱ መሰናክል እየሆነ ይገኛል፡፡

የሚከተሉት ጥቅሶች ሰብዓዊው ፍጡር ስለተፈጠረበት ዓላማ ምን ያስተምራሉ? ዘፍ. 1:26—28፣ መዝ. 8:3—8፣ ኢሳ. 43: 6-7--"ለክብሬ የፈጠርኩትን" (ኢሳ. 43፡7) ሲል ምን ማለቱ ነው? "ለክብሬ" የተሰኘው ቃል ከፍጥረቱ ግዛት ጋር እንዴት ይዛመዳል?

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

በዘፍጥረት ከቀረበው ጥቅስ መመልከት እንደምንችለው እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ለመፍጠር ሌሎች የተለዩ ምክንያቶች ሊኖሩት ቢችሉ እንኳ በምድር ላይ ሥልጣን እንዲኖራቸውና እንዲገዟት መፈጠራቸው ግን እሙን ነው (ዘፍ. 1፡26- 28)፡፡ የመጀመሪያዎቹ ጥንዶች በከፍታ የሚገኘው አምላካዊ ክብርና ሥልጣን መተላለፊያ መስመር በመሆን ምድርንና ሙላቷን በመጠበቅ፣ በመንከባከብና በማስተዳደር የእግዚአብሔርን ክብርና ጸባይ በአንድነት ያንጸባርቁ ነበር (ራእ. 1፡5-6)፡፡ ኃጢአት ባይነሳ--በእነርሱ ይገለጥ የነበረውን አምላካዊ ክብርና ምድርን የመግዛት ሥልጣናቸውን ስፋትና ጥልቀት ማወቅ በተቻለ ነበር፡፡

በየሱስ ላይ ባለን እምነት፣ ሕይወታችንን በእምነትና በመታዘዝ ለእርሱ በማስገዛትና ከእርሱ ጋር ኅብረት በመፍጠር ከዳዊት ጋር "እግዚአብሔር በእኔ ላይ ያለውን ዓላማ ይፈጽማል" (መዝ. 138፡ 8) ማለት እንችላለን፡፡ በተለይ የእርሱ ፈቃድ በእኛ ውስጥ እንዲፈጸም ራሳችንን ለእርሱ አሳልፈን ስንሰጥ እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ዓላማ እንዳለው እንረዳለን--ይህም ልበ ሙሉና ደስተኞች እንድንሆን መንስዔ ይሆነናል፡፡ አንድ ሰው ወደ እርስዎ መጥቶ "እንደ ክርስቲያን የህይወትዎ ዓላማ ምን ይመስላል?" ብሎ ቢጠይቆት መልስዎ ምን ይሆናል? ለምን?

## ምድርን የመግዛት ልዩ መብትና ጥቅም

በዘፍ. 1፡26-28 ሰዎች በምድር ላይ እንዲኖራቸው የተሰጣቸው “ሥልጣን” ምንድን ነው?

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
---

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
---

ሥልጣን የተሰኘው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ምንጭ የዕብራውያኑ ግስ ራዳህ ሲሆን፤ በበላይ ሆኖ የመግዛትንና የማስተዳደርን ልዩ መብትና ኃላፊነት ያመለክታል። ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለበት ይህ ዐወደ ምንባብ ሰብዓዊው ዘር በማንኛውም ፍጥረት ላይ ያለውን የላቀ ሥልጣንና የሥልጣን ደረጃ ያመለክታል። ሆኖም ይህ ሥልጣን በቅንነት ይሁን በክፋት እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል ግሱ በቀሪዎቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ራሱን በራሱ ሲገልጽ አይስተዋልም። ሥልጣን ከተፈጥሮ ጋር የነበረው ቁርኝት ከቅንነትና ከበጎ በተጎዳኘ መልኩ እንደ ነበር ከኃጢአት ውድቀት አስቀድሞ የነበረው እንከን የለሽ ተፈጥሮ ሹክ ይለናል።

እግዚአብሔር ምድርን ግዟት ሲል በዘፍ. 1፡28 የተናገረው ቃል ወደ ተመሳሳይ ድምዳሜዎች ለመድረስ ያስችለናል። ግዟት--በሚል ጥቅም ላይ የዋለው ካቫሽ የተሰኘው የዕብራውያን ግስ፤ ሰዎች ምድርን በበላይ እንዲገዙና እንዲያስተዳድሩ የተሰጣቸውን ሥልጣንና የሥልጣን እርከን ያመለክታል። በብሉይ ኪዳን በሌሎች ስፍራዎች--በተጨባጭ በቁጥጥር ስር ስለ ማዋል የሚገልጸው ይህ ግስ (ካቫሽ) ቀደም ባለው አንቀጽ ከተመለከትነው ራዳህ ይልቅ ጥንካሬ አለው (ዘኁ. 32፡22፣ 29፣ ኤር. 34፡11፣ 16፣ አስቴ. 7፡8፣ ነህ. 5፡5)። ከእነዚህ ታሪኮች በአብዛኞቹ በግልጽ ይስተዋል የነበረው ሥልጣንን ያለ አግባብ የመጠቀም አባዜ እግዚአብሔርን ደስ አለማሰኘቱ ተወስቶአል። ነገር ግን መለስ ብለን በፍጥረት ታሪክ ለቀረበው ዐውደ ሀሳብ አጽንኦት በመስጠት ትኩረታችንን ምድርን እንዲገዙ በእግዚአብሔር መልክ ወደ ተፈጠሩት ኃጢአት የማያውቁ ጥንዶች ስናደርግ፤ ይህ ምድርን የመግዛት ሁኔታ--በፈጣሪ ቦታ ተሰይመው የሚሰጡትና ቅን የሆነውን የአገልግሎት ባህሪ ብቻ የተላበሰ እንደሆነ እንመለከታለን።

እግዚአብሔር አዳምን በኤደን የአትክልት ስፍራ በማስቀመጥ እንዲያለማት፣ እንዲንከባከባት፣ እንዲያገለግላት፣ በቅርብ ሆኖ እንዲከታተላትና እንዲጠብቃት (ዘፍ. 2፡15) ማድረጉ ምድርን ስለ መግዛት ተጨማሪ ጥልቀት ያለውን ጽንሰ ሀሳብ ይሰጠናል።

ይህን በአእምሮአችን መያዝ ስንችል መግዛት የተሰኘው ቃል መንከባከብና በፍቅር መመገብ ወይም ማስተዳደር የሚል ፍቺ እንዳለው እንገነዘባለን። እግዚአብሔር ለፍጥረታቱ ያለውን መለኮታዊ ፍቅር ያንጸባርቅ የነበረው የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን የመግዛት ሥልጣን ሐብትም ሆነ ኃይል ምንጩ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው ግንኙነት ነበር።

ዛሬ፣ ዛሬ መግዛት የተሰኘው ቃል ፍቺ ከአዎንታዊው ይልቅ አሉታዊ አንደምታው ሚዛን ደፋና ከመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ ጋር ተለያየ። ከኃጢአት ውድቀት አስቀድሞ ጥቅም ላይ ከዋለው ከዚህ ቃል አንዳንድ መርኅዎችን ወስደን በማናቸውም "በምንገዛቸው" ነገሮች ላይ ልንተገብር የምንችላቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?

*ማክሰኞ ሰኔ 28* *Jul 5*

# ወሰን

ሰብዓዊው ፍጡር "በምድር ሁሉ ላይ" (ዘፍ. 1፡26) ሥልጣን ይኑረው መባሉ ግዛቱ ወሰን የለውም ማለት ይሆን? ግዛት (በተጨማሪ "መጋቢነት" በሚል የሚስተዋል ሲሆን) ወሰን ሊኖረው እንደሚገባ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ፍንጭ ይሰጣል።

ለምሳሌ መልካምና ክፉን የሚያሳውቀው ዛፍ አዳም ከሚያስተዳድረው ወሰን ውጪ መሆኑን እግዚአብሔር ነግሮት ነበር (ዘፍ. 2፡15-17)። ስለዚህ የመጀመሪያው ኃጢአት ከመጋቢነት ዐውድ ጋር ትስስር ነበረው። አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ወሰን ጣሱ። ይህ የወሰን ጥሰት ፍጥረት ሁሉ ዛሬ ድረስ እንዲማቅቅ መንስኤ ሆኖአል (ሮሜ 8፡20-22)።

በዘፀ. 20፡1-17 በእግዚአብሔር ሕግ የቀረቡልን "ግዛቶች" ምን ይመስላሉ? ሕጉ ስለ ሰብዓዊው የግዛት ወሰን ምን ይነግረናል?

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------

በሰይጣን ኃይል ስር የዋሉ ሕዝቦች ሕጋዊ ባለ መብት ያልሆኑበትን፣ ከቁጥጥራቸው ውጪ የሆነውን ነገር በስራቸው ለማስገዛት (ለምሳሌ በዘፀ. 1-14 የተጠቀሰው ፈርዖን፣ በማቴ. 2 የምናገኘው ሔሮድስ) ያደርጉ የነበረው አሳዛኝ መፍጨርጨር እስከ ዘመን ፍጻሜ (ራዕይ 13) የሚቀጥል የሰው ልጆች ታሪክ ነው። ራሱን "የዚህ ዓለም ገዥ" (ዮሐ. 12፡31) በማድረግ ሥልጣን የተቆናጠጠውን የሰይጣንን ባህሪ ያንጸባርቃሉ። ሥልጣንን አጭበርብሮ እጁ የሚያስገባ--ሌሎችን በኃይል የሚቆጣጠር ጁንታ ይሆናል።

በሌላ በኩል ሥልጣን እንዲኖራቸው በሚፈልጉት ነገር ላይ የበላይነታቸውን የማይቀበሉ አሉ (ማቴ. 25፡14-30፣ ሉቃስ 19፡12-27)፤

ኃጢአት ሰብዓዊው ፍጡር በተፈጠረበት ወቅት ተሰጥቶት የነበረውን የሥልጣን መጠን እንዲያጣ መንስኤ ቢሆንም፤ ነገር ግን ተሰጥቶን ከነበረው ላይ ሁሉንም አላጣንም። የየግል ኃላፊነቶቻችንን አስመልክቶ አያሌ ነገሮች ዛሬም በየግል ቁጥጥራችን ስር ይገኛሉ። ለምሳሌ ክርስቶስ የግል ህይወታችን እንድንገዛ ማስቻሉ (1ቆሮ. 9፡ 25-27. ገላ. 5፡22-23)፣ ለምድራችንና በውስጧ ለሚገኙ ፍጡራን የምናደርገው ጥንቃቄ እንዲሁም ከእግዚአብሔር የተትረፈረፈ በረከት መቀበላችን (ያዕ. 1፡17፣ ማቴ. 25፡14-30) እንደ አብነት የሚቆጠሩ ናቸው። እንደ ክርስቲያን-- የኃላፊነት ወሰኖቻችንን በሚገባ ማስተዋልና በእነዚህ ክልሎች ውስጥ ታማኝ መጋቢዎች ሆነን

መሥራት ይጠበቅብናል።

በእርስዎና በቤተሰብዎ፣ በጓደኞችዎ ወይም በሥራ ባልደረቦችዎ መሀል ባሉ ግንኙነቶች በተለይ እንዲያከብሯቸው ሆነው ቁልጭ ብለው ከተቀመጡ ወሰኖች አንዳንዶቹ የትኞቹ ናቸው? ስለነዚህ ወሰኖች ምንነት በቂ ግንዛቤ እንዲኖረን ምን ዓይነት መርኆዎችን ጥቅም ላይ ማዋል እንችላለን? (ማቴ. 7፡1፣ 12)።

*ረቡዕ ሰኔ 29* *Jul 6*

# ምድርን መንከባከብ

"እግዚአብሔር አምላክ ሰውን ወስዶ እንዲያለማትና እየተንከባከበ እንዲጠብቃት በዔድን የአትክልት ስፍራ አስቀመጠው" (ዘፍ. 2፡15)። ለምድራችን ጥንቃቄ ማድረግ በሚገቡን ነገሮች ዙሪያ ከጥቅሱ በአርአያነት ልንወስዳቸው የሚገቡ መርኆዎች ካሉ ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-ኃጢአት ከመግባቱ አስቀድሞ እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን የመላው ፍጥረቱ መጋቢ አድርጎ ሾሞአቸው ነበር። በዚህም በእንስሳትና ዕጸዋት ሥነ ሕይወት ዙሪያ ጥልቅ ዕውቀት ነበራቸው። ነገር ግን ኃጢአት ከገባ በኋላ እነርሱ በእግዚአብሔር ያመጹትን ያህል መላው ፍጥረት በእነርሱ ላይ አመጻ ያደረገ መሰለ። ሰብዓዊ ፍጡራን ራሳቸውን በእያንዳንዱ ነገር (በአየር ጸባይ፣ በግብርና ሥራ፣ በእንስሳት ዓለም) ፊት ደካማ ሆኖ አገኙት።

"አዳም ዝቅ ባሉት ፍጥረታት ላይ የተሰጠውን የንጉሥነት ስያሜ እንደ ያዘ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ በቀጠለ መጠን ይህን የበላይነት መላው ፍጥረት ተቀብሎ መተዳደሩ አንድና ሁለት አልነበረውም። ሆኖም አምላካዊውን ቃል በተላለፈ ጊዜ ያ በበላይነት ያስተዳድረው የነበረ ግዛት ከእጁ አፈተለከ። እርሱ ራሱ የከፈተው የአመጻ መንፈስ ወደ መላው እንስሳት ተዛመተ። በዚህም የሰው ህይወት ብቻ ሳይሆን የእንስሳቱ ተፈጥሮ፣ ደኑ፣ የመስኩ ሣርና ይተነፍሱት የነበረ አየር ሳይቀር--በጥቅሉ አሳዛኙን--ክፉ የማወቅ አስተምህሮ ሹክ የሚሉ ሆኑ።"–Ellen G. White, Education, pp. 26, 27.

ዛሬ በምድራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ በሚሄድ ፍጥነት የተፈጥሮ ጥፋት ሲደርስና እንስሳት እርስ በርሳቸው እንዲሁም ከዕጸዋት ጋር ያላቸው መስተጋብር እየከሰመ ሲሄድ ምስክር እየሆንን ነው። ራሳችንን ከዚህ አሳሳቢ ውድመት ለመከላከል ብሎም ለመጠበቅ ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ለማዋል ብርቱ ጥረት በማድረግ ላይ እንገኛለን። ምንም እንኳ ቴክኖሎጂና የቴክኖሎጂ ግስጋሴ ራሳችንን ከዚህ አደጋ ለመጠበቅ ቢረዳንም፤ አልፎ አልፎ ይኸው ቴክኖሎጂ በፕላኔታችን ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል። በተለይ ምድርን ለአደጋ የማጋለጡ አካሄድ በሌሎች ህልውና ላይ አስጨናቂ ሁናቴዎችን ሲፈጥር እንስሳት እርስ በርሳቸው እንዲሁም ከዕጸዋት ጋር ያላቸው መስተጋብር--የሞራል፣ የሐቀኝነት (የሥነ ምግባር)፣ እና የመንፈሳዊ ርዕሰ ጉዳይ ይሆናል።

“ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች ልጓም የለሹን ከመጠን በላይ የማግበስበስና የማባከን አሰልቺ የዕለት ከዕለት ሕይወት በመቃወም ችግር ዐልባውን፣ የተመጠነና ጤነኛ የአኗኗር ዘይቤ አጥብቀን እንደግፋለን። ሰዎች ለፍጥረት ክብር እንዲሰጡ፣ የምድርን የተፈጥሮ ሐብት በቁጠባና በአግባቡ እንዲጠቀሙ፣ አንድ ሰው-- ያስፈልገኛል ያለው ነገር በእርግጥ ያስፈልገው እንደሆነ ደግሞ ደጋግሞ እንዲያጤንና ለፍጥረት ተገቢውን ክብርና ማዕረግ እንዲሰጥ ጥሪ እናደርጋለን።” Official Statement of the Seventh-day Adventist Church on Environ- ment, 1995.

የአካባቢያችን መልካም መጋቢ እንድንሆን የተጣለብንን ኃላፊነት በአግባቡ እየተወጣን፤ በተመሳሳይ ለምድር በአደጋነት የተጋረጡ ነገሮችን እንዲሁም በዙሪያችን ያሉ ፍጡራንን እንደ አማልክት የመመልከቱን አባዜ እያስወገድን፤ ለምድር ያለንን አመለካከት ሚዛናዊ አድርገን መጠበቅ የምንችለው እንዴት ነው? በሮሜ. 1፡25 የተሰጠን ማስጠንቀቂያ ምን ይመስላል?

*ሐሙስ ሰኔ 30* *Jul 7*

## የተነጥቅነውን “ግዛት” ማስመለስ

በኃጢአት መውደቅ የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን ዔድን የግዛታቸው አካል የመሆኗን ልዩ መብትና ጥቅም ማጣታቸውን ጨምሮ እኛን ሰብዓዊ ፍጡራንን ለብርቱ እጦት ዳርጎናል።

ክርስቶስ ለእኛ ያደረገው ነገር ግድ ብሎን እኛም ወደ ሌሎች በመድረስ በእርሱ የተሰጡንን ሌሎችም የግላቸው እንዲያደርጉ የበኩላችንን እንድንሠራ በእግዚአብሔር ተጠርተናል። ምንም እንኳ ይህ የማያቋርጥ ሂደት እስከ ክርስቶስ ዳግም መገለጥም ሆነ ከዚያ ባሻገር የሚቆም ባይሆንም በእጦት ወዳሉ፣ ወደ ጠፉና ከቃሉ እጥረት የተነሳ ወደ ተዳከሙ በመድረስ ዛሬ ልንሠራ የምንችላቸው አያሌ ተግባራት አሉ። ወደ ሌሎች በመድረስ በችግር ያሉ ወገኖችን መታደግ ስንጀምር የጠፋው ከአሁን ጀምሮ ወደ ቀድሞ ንጽህናው ይመለስ ዘንድ እግዚአብሔር ሊጠቀምብን ይችላል።

ከዚህ በታች የቀረቡት ጥቅሶች ሰዎች በኃጢአት ምክንያት ካጡት “ግዛት” ጥቂቱን ዳግም የግላቸው ማድረግ እንዲችሉ እንዴት ሊረዳቸው ይችላል?

ዘዳ. 15፡7—12 ______________________________________________________________________

ሉቃስ 14፡12—14_ 1ጴጥ. 3፡15_ ያዕ. 1፡27

___________________________________________________________

ኢሳ. 58፡7____________________________________________________________________________

2ተሰ. 3፡10

______________________________________________________________________

እንደ ቤተ ክርስቲያን አካል እንድናደርግ የተጠራንባቸው አያሌ ተግባራት ያሉ ሲሆን ከነዚህም አንዱ በችግር ወዳሉ ወገኖች መድረስ ነው። ምግብ፣ ልብስ ወይም መጠለያ--ፋታ በማይሰጥ ችግር ውስጥ ለሚገኙ ወገኖች እጅግ አንገብጋቢ የሚሆኑባቸው ጊዜያቶች ይኖራሉ። በሥቃይ ውስጥ ለሚገኙ ወገኖች ፍቱን መድኃኒት የመሆን አስፈላጊነት አጠያያቂ ባይሆንም ነገር ግን በሕይወታቸው አጥተውት የነበረውን ግዛት ዳግም ባለቤት የሚያደርጋቸው--ከማስታገሻው ባሻገር የሚሰጥ እርዳታ በእጅጉ አስፈላጊ ነው።

በውስጣችን ያለውን ተስፋ ለሌሎች ለማካፈል ሁልጊዜም በተነሳሽነት የተሞላ ዝግጁነት ሊኖረን የተገባ ቢሆንም የወገኖችን ቁሳዊ ፍላጎት የትና መቼ በመቅረፍ ወደ ተሻለው የኑሮ ዘይቤ ማመላከት እንዳለብን መሥራት ይጠበቅብናል። ምንም እንኳ በእጦት ያሉ ሰዎች ችግር ፈርጀ ብዙ--የሚያሹአቸውም ነገሮች ልዩ ልዩ ቢሆኑም ለማኅበረሰባችን ብርሃን፣ የፈውስ ምንጭና ተስፋ እንድንሆን በእግዚአብሔር ተጠርተናል። ይህ ደግሞ ለምናገለግለው አፍቃሪና አዳኝ አምላክ ለዓለም ምስክር መሆን ምን ማለት እንደሆነ ገልጠን የምናሳይበት አስፈላጊ ክፍል ነው። በእጦት ላሉ ወገኖች እንደ ወደብ መብራት--የብርሃን ጨረር የምንፈነጥቅና የተስፋ ጭላንጭሎች በመሆን ጌታ በሚሰጠን ኃይል የምንችለውን ሁሉ መሥራት ይኖርብናል። እንደ ክርስቲያን ከእኛ አነስተኛ ተግባር አይጠበቅም። ይህን የአገልግሎት ሚና በአግባቡ ስናከናውን ሰዎች እግዚአብሔር እንዴት ያለ አምላክ እንደሆነ ዐይኖቻቸውን ገልጠው መመልከት እንዲችሉ እንረዳቸዋለን። ለቁሳዊው እጦታቸው አስፈላጊ የሆነውን አገልግሎት ስንሰጣቸው መንፈስ ቅዱስ ወደ ልቦቻቸው መድረስ የሚችልበትን መንገድ እንጠርጋለን። የሱስ ያደረገው ይህን ነበር። እኛም በተመሳሳይ ይህን አገልግሎት እንድንሰጥ ተጠርተናል።



## ተጨማሪ ሀሳብ

የሚከተሉትን መልእክቶች ያንብቡ፡ Ellen G. White, “Temperance and Dietetics,” pp. 202—206; “Discipline,” pp. 287—290, in Education; “Need for Self-Mastery,” pp. 73, 74, in Counsels on Diet and Foods; “The Principles of Stewardship,” pp. 111—113; “Sharing in the Joys of the Redeemed,” pp. 348—350, in Counsels on Stewardship.በከፍተኛ ውድቀት በተዘፈቀ ዓለም ውስጥ ከመኖራችንና ነገሮችን ከርቀት ከመመልከታችን አኳያ በውድቀት ያጣነውን ለመገመት ቀላል ሊሆን አይችልም። እኛ የምናውቀው የዚህን ክፉ ዓለም ገጽታ ብቻ ነው። ስለ መጀመሪያ አፈጣጠራችን፣ ስለ ኃጢአት አጀማመር፣ ስለ ሞትና ስለ ክፉው መንሰራፋት የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ ባያስቀምጥልን ኖሮ ሁሉንም የራሱ የህይወት አካል አድርገን ያለ ማወላወል በጸጋ በተቀበልን ነበር። ነገሮች በእርግጥ አሁን የያዙትን መልክ መያዝ እንዳልነበረባቸው የውድቀት ታሪክ ያሳየናል።

አዳምና ሔዋን ምድርን የመግዛት ሥልጣን ተሰጥቶአቸው እንደ ነበር የዘፍጥረት መጽሐፍ ይነግረናል። ሆኖም ኃጢአት ሲሠሩ በመለወጣቸው ከምድር ጋር የነበራቸውም ግንኙነት ተለወጠ። የምድር ገጽታም እንዲሁ የተለየ መልክ ያዘ። አዳምና ሔዋን በምድር ላይ የነበራቸውን ሥልጣን በድንገት አጡ። የመተላለፍ መዘዙም ግዙፍና የከፋ ሆነ። “የምድር እሾኽና አሜከላ ማብቀል፡ ዘፍ. 3፡17-18)፣ የጥፋት ውሃ (ዘፍ. 7፡12)፣ ጭልጥ ያለ በረሃና ያገጠጠ ምድረ በዳ፣ በምጥ ጊዜ እንዳለው ሥቃይ የዓለም መቃተት (ሮሜ 8፡19-22) የኃጢአትን ውጤት ተከትሎ ምድር ከያዘችው ገጽታ ከብዙው በጥቂቱ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ

ያስቀምጥልናል”–Handbook of Seventh-day Adventist Theology (Hagerstown, Md.: Review and Herald® Pub. Assn.), vol. 12, p. 254. የጠፋውን ሁሉ ወደ ቀድሞው ንጽህና ለሚመልሰውና ካለፈው ወይም ከአሁኑ በበለጠ ለወደፊቱ ተስፋ ለሚሰጠን ለአምላካዊው የደኅንነት እቅድ አብልጠን አምስጋኞች ልንሆን ይገባል።

## የመወያያ ጥያቄዎች:

1. ምንም እንኳ የእነዚህ ጥቅሶች ዐውደ ሃሳብ (ዘፀ. 23:10—12፣ ዘዳ. 11:11-12፣ 20:19-20) ከዛሬው የተፈጥሮ ሳይንስ አረዳድ ጋር ቀጥተኛ ትስስር ያለው ባይመስልም ለአካባቢያችን መልካም መጋቢ ለመሆን የሚያስፈልጉንን ነገሮች በማስተዋሉ ረገድ ምን ዓይነት መርኅዎችን መውሰድ እንችላለን? በተጨማሪ ከአካባቢ መጋቢነት ወደ ተፈጥሮ አምላኪነት አልፈን መሄዳችንን እንዴት ማወቅ እንችላለን?
2. አሁን ስለምናውቃት ምድር ተፈጥሮአዊ ሁኔታ ያስቡ። የትኛው ጎልቶ ይታያል--ወዳጅነቷ ወይስ ጠላትነቷ? መልስዎን እንዴት አመክንዮአዊ አድርገው ማቅረብ ይችላሉ?
3. በእሑድ ጥናት መጨረሻ ላይ በሰብዓዊው ፍጡር ህይወት ትርጉምና ዓላማ ዙሪያ በተነሳው ጥያቄ ላይ ተወያዩ። ይህን ጥያቄ ለሚጠይቆ ሰው የሚሰጡት መልስ ምን ይሆናል? መልሶቻችን በእግዚአብሔር ወይም በደኅንነት ላይ እምነት ከሌላቸው ሰዎች እንዴት ሊለይ ይችላል?
4. መግዛት የተሰኘው ቃል የቀደመ ትርጉሙን ሳይለቅ ዛሬም ጥቅም ላይ ማዋል የምንችለው እንዴት ነው? ያ ማለት--መጀመሪያ ላይ ምድርን መግዛት መልካም የነበረው ለምንድን ነው? ዛሬም በተመሳሳይ መተግበር የሚችለውስ እንዴት ነው?